# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ቴክኒካል ድጋፍ

(ክፍል ሁለት)

ጥላሁን ጌታነህ

ሰላም! ጤና ይስጥልን ውድ የዚህ ትምህርታዊ አምድ አንባቢዎች! ባለፈው ሳምንት ‹‹ የማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፋያ ጣቢያዎች ቴክኒካል ድጋፍ›› በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ኤልክትሪክ ኃይል የማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ኦፕሬሽን ዘርፍ የቴክኒካል ድጋፍ መምሪያ ዳይሬክተር ከሆኑት አቶ አበባው ያለው ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ በክፍል አንድ ዝግጅታችን ማስነበባችን ይታወሳል። በዛሬው ዝግጅታችንም የዚህኑ ቃለ ምልልስ ሁለተኛ ክፍል የምናቀርብላችሁ ይሆናል። መልካም ንባብ!

ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን፡- የሥራ ክፍሉ እስካሁን ምን ምን ሥራዎችን አከናውኗል?

አቶ አበባው፡ መምሪያው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ለአብነትም ጉዳት የደረሰባቸውን ዕቃዎች በመለየት ያልተሟሉ ዶክመንቶች ከቦታው ድረስ በመሄድ እና በመሰብሰብ አሁን የሚኖራቸው ተመን ከዲዛይን ክፍል ዋጋ በማያያዝ የመድን ክፍያቸው እንዲፈጸም ወደ ኢንሹራንስ ክፍል የመላክ ሥራ ሰርተናል። ለትራንስሚሽን ሰብስቴሽን ኦፕሬሽን ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ፕሮሲጀሮችን፣ ደረጃዎችንና ፖሊሲዎችንም እያዘጋጀን ነው። በትራንስሚሽን ሰብስቴሽን ኦፕሬሽን ስር ያሉ ሀብቶችን የመመዝገብ በቂ መለዋወጫ መኖሩን ለማረጋገጥ የመለዋወጫ ግዥን በማጥናት ግዢ እንዲፈጸም ለማድረግ ግብዓት እንዲሆን መጠይቅ በመበተን ሰብስበናል። ለሪጅኖች የሚሆኑ 7 ፕሮሲጀሮችንም አጸድቆ ለሥራ እንዲሆኑ ወደ 13ቱም ሪጅኖች የማውረድ ሥራ ሰርቷል።

በሌላ በኩል አየር መንገድ ከአሁን ቀደም ወረገኑ ከሚባለው ማከፋፈያ ጣቢያ ኃይል ሲያገኝ የነበረ ቢሆንም የኃይል መቆራረጥ እያጋጠመው በመቸገሩ በራሱ ትልቅ ወጪ አውጥቶ 132 ኪ.ቮ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ሠርቷል። ይሄን ጣቢያ ሲሰራ ኦፕሬተሮች፣ ጣቢያው ውስጥ ያለውን እቃ የሚቆጣጠር ኢንስፔክሽን እና የጥገና ባለሙያዎች ይፈልግ ነበር። እኛም የኃይል ሽያጭ ስምምነት፣ በSLA የኦፕሬሽን፣ የጥገናውንና የኢንስፔክሽን ሥራውን የሚሠራ ዓመታዊ ኮንትራት ወስደን አገልግሎት እየሰጠን እንገኛለን። በተመሳሳይ የራሳቸውን የማከፋፈያ ጣቢያ ለገነቡ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች፣ ኢንዱስትሪዎችና ትልልቅ ድርጅቶች ኮንትራት ወስደን እየሰራን ነው።

ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን፡- የመምሪያው መደራጀት ለተቋሙ ምን ጠቀሜታ አስገኝቷል? ምን ችግሮችን ሊቀርፍ ችሏል?

አቶ አበባው፡ መምሪያው መደራጀቱ የPSLA የውል ሰነዶችን በመመርመር ቴክኒካል ግብዓቶች በመስጠት፣ ለኃይል ማስተላለፊያ መስመርና ማከፋፈያ ጣቢያ ኦፕሬሽን ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የአሠራር ሂደቶችን በማውጣት ወጥ የሆነ አሠራር እንዲኖር በማድረግ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን አድርጓል። የተበላሹ ዕቃዎችን፣ ማሻሻያ የሚፈልጉ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎችን በማጥናትና በመጠገን ከፍተኛ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና የማከፋፈያ ጣቢያዎች ያለብልሽት በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩም እየተደረገ ነው። አሁን ላይ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች እና የማሰራጫ መስመሮች ሲቆረጡ የተቆራረጡ መስመሮችን እና ያደረሱትን ጉዳት እንዲሁም ያልተሸጠ ኃይል የሚመዘግብ “ኢኢፒ ሳውዝ ክላውድ” የሚባል ሶፍትዌር በክፍሉ ሠራተኞች ዳብሮ ሥራ ላይ አውለናል። መምሪያው ዳታ ቤዝ በማዘጋጀት በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ዕቃዎችን እየመዘገበ የሚገኝ ሲሆን ሪጅኖች ያሉባቸውን የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት በማጥናት ዋናው ፓወር ትራንስፎርመሩ አደጋ እንዳይደርስበት የሚከላከሉ 40 እርዚንግ ትራንስፎርመር እና 46 ሺ ሜትር የፓወር ኬብል ገመድ ግዥ ለመፈጸም በሂደት ላይ ይገኛል።

ከዚህ በፊት በግሪድ ውስጥ ላሉ ዕቃዎች በሙሉ መድን እየተገባ አላስፈላጊ ወጪ ስንከፍል ቆይተናል። አሁን ክፍሉ ከተቋቋመ በኋላ መድን የሚገቡ ዕቃዎች ተለይተው እንዲገቡ እያደረግን ነው። በተጨማሪም የመድን ድርጅቶች የሚጠይቋቸውን መረጃዎች አደራጅቶ ባለመስጠት ክፍያ ሳናገኝ የምናቀርባቸው ጉዳዮች ብዙ ነበሩ። አሁን ግን መረጃዎች በአግባቡ ተጠናክረው የሚሰጡበትን አሰራር ዘርግተናል። በዚህም ሁሉም ሪጅኖች ወጥ በሆነ መንገድ ኢንስፔክሽን፣ ጥገናና ድንገተኛ ሥራዎችን መቼ መስራት እንዳለባቸውና ሥንት ሰው መሳተፍ አለበት የሚለው ወጥ አሰራር የተዘረጋ ሲሆን በዚህም ከፍተኛ ወጪ መቀነስ ችለናል።

ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን፡- መምሪያው የቴክኒካል ድጋፍ ሥራው የኦፕሬሽን ሥራዎች አስተማማኝ እንዲሆኑ እና የጥገና ሥራዎችን ለማቀላጠፍ እያደረገ ያለውን አስተዋፅዖ ቢያስረዱን?

አቶ አበባው፡ የኦፕሬሽን ሥራዎች አስተማማኝ እንዲሆኑ ፕሮሲጀሮችን፣ ስታንዳርዶችን፣ ፖሊሲዎችን በስልክ፣ በደብዳቤና በዋትስአፕ ቡድን በሚገኙ መረጃዎች በማጋራት አስተዋፅዖ እያደረገ ይገኛል። በተጨማሪም አር ቲ ኢ ኢንተርናሽናል ከሚባል የፈረንሳይ የትራንስሚሽን ካምፓኒ ጋር “ግሪድ ሞደርናይዜሽን” የሚባል ፕሮጀክት ተቀርጾ እየተሰራ ነው። ካምፓኒው እንዴት እየሰራ ነው የሚለውም ፈረንሳይ ድረስ ተሂዶ የልምድ ልውውጥ የተደረገ ሲሆን ካምፓኒው “SAP plant maintenance module” የሚባል እስከ ሴሪያል ቁጥር ድረስ የወረደ የድርጅቱን ንብረት የሚመዘግብ አሰራር ተግባራዊ እያደረገ ሲሆን ለዚህም ፕላንት ሜንቴናንስ ለሚባለው የሳፕ ሞጁል ዳታ የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው። በተመሳሳይ ኬኒያ ካለው አሞቴክ አፍሪካ ከሚባል ድርጅት ጋር የትራንስፎርመርና ሌሎች ዕቃዎች ፍተሻ ሥራ ዙሪያ ለተለያዩ መሃንዲሶች ስልጠና እየሰጠ ሲሆን ይህም የኦፕሬሽን ሥራዎችን አስተማማኝ በማድረግ በኩል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው።



አቶ አበባው ያለው

ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን፡- ለሰጡን መረጃ ከልብ እናመሰግናለን!

አቶ አበባው ፡- እኔም አመሰግናለሁ!